በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ

## ክፍል ሦስት

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ግንቦት ፲ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

## *የጋብቻን ሕይወት (የትዳርን) ምንነት መረዳት*

- **ባሎች ሚስቶቻቸውን እየጎዱም ቢሆን ራስ በመሆናቸው መከበር ይገባናል ብለው ማሰባቸው የሚመነጨው የጋብቻን ሕይወት ትርጉም በአግባብ ካለመረዳት ነው፡፡**
- **ሚስቶችም ከባሎቻቸው የተሻለ የተማሩ በመሆናቸው ወይም ላቀ ያለ የኢኮኖሚ አቅም ስላላቸው ብቻ እኩል ነን የሚለውን ብቻ በመውሰድ ባሎቻቸው ዘወትር የሐሳባቸው ተገዢ እንዲሆኑላቸው የሚፈልጉ ሆነው ይገኛሉ፡፡**
- **ይህን በመሳሰሉ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች የተነሳ በርካታ ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡ ስለዚህ ተጋቢዎቹ የጋብቻውን ሕይወት (የትዳሩን) ምንነት በአግባብ መረዳት ይገባቸዋል፡፡**
- **መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶችን** ‹‹ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፡፡» ***ኤፌ 5፡22፡፡*** ይላል፡፡ ይህም ሚስቶችን ለጌታ እንደምትታዘዙት ለባሎቻችሁ ታዘዙ ተገዙ ማለቱ ነው፡፡ ምክንያቱም «ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና።» ***ኤፌ 5፡23፡፡***
- ምስጢረ ተክሊል ሲፈጸምም ካህኑ ለሙሽራይቱ « አንችም የተባረክሽ እህት የታደልሽ ሙሽራ ሆይ ባልሽን የመከርሁትን ምክር ሁሉ እንደሰማሽ አንችም ደግሞ ልታከብሪውና ልትፈሪው ይገባል፡፡ ከፈቃዱ ከትእዛዙ ልትተላለፊ አይገባሽም፡፡ እንዲያውም እሱን ባዘዝሁት ሁሉ እጥፍ አድርገሽ ፈቃዱን ልትፈጽሚ ይገባሻል፡፡ … እናታችን ሣራ ከአባታችን ከአብርሃም ጋራ እንደ ነበረች ጌታዬም ትለው እንደ ነበር ፈቃዱን መፈጸሟን አይቶ ልዑል እግዚአብሔር እንደባረካትና የሱንም ፍቅር አግኝታ ከርጅናዋ በኋላ ይስሐቅን ወለደች፡፡» የሚለውን ትእዛዝ ያነብላታል፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

***የጋብቻን ሕይወት (የትዳርን) ምንነት መረዳት***

- እናታችን ሣራ አብርሃምን በማክበር፡-
    - አብርሃም ዘመዶቹንና ያለውን ሁሉ ትቶ ሲወጣ እርስዋም ዘመዶችዋንና ያላትን ሁሉ ትታለች
    - አብርሃም በነገራት መሠረት እህቱ ነኝ ብላ መልሳለች
    - ታደርግለት ዘንድ የጠየቃትን ሁሉ ከአንድ ጊዜ ብቻ በቀር ሳትጠይቀው ፈጽማለጻለች
- ባልን የማክበር ትእዛዝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያናችን ለዘመናት ሲፈጸም የኖረ ታሪካዊ ትእዛዝ ነው፡፡
- ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ሚስቶችን ይታዘዙ ዘንድ ከሰጠቻቸው ትእዛዝ አስቀድማ ባሎችን በምስጢረ ተክሊል በካህኑ አማካይነት ‹‹አንተ የተባረክህ ልጅ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የጸናህ የተወደድህ ወንድም ሆይ በዚህች በተባረከች ሰዓት በጥሩ ልቡና በንጹሕ ኅሊና በመልካም አሳብ ሚስትህን መቀበል ይገባሃል፡፡ የሚጠቅማትን ነገር ሁሉ ለመሥራት በርታ፡፡ የምታዝንላትም ሁን፡፡ ልቡናዋን ደስ የሚያሰኛትን ነገር ሁሉ ለመሥራት አፍጥን፡፡ ከእናት ከአባቷ በኋላ ዛሬ በሷ ላይ አለቃ አንተ ነህና፡፡ … ›› በማለት አዛለች፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

***የጋብቻን ሕይወት (የትዳርን) ምንነት መረዳት***

- **ስለዚህ ባሎች ሆይ አስቀድማችሁ እንደታዘዛችሁ ሚስቶቻችሁን ደስ የሚያሰኛቸውን በመፈጸም እነርሱም የራሳቸውን ኃላፊነት ይወጡ ዘንድ ትፋጠናላችሁ?**
- ***መጽሐፍ ቅዱስ*** ‹‹ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፡፡›› ***ኤፌ 5፡25፡፡***
- **ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ለክርስቶስ እንደሰጠች ሚስቶችም ለእግዚአብሔር ራሳቸውን እንደሚሰጡ አድርገው ራሳቸውን ለባሎቻቸው እንዲሰጡ እንጠይቃቸዋለን፡፡**
- **ባሎች ሆይ አስቀድሞ ራሱን የሰጠ ማነው? ክርስቶስ ወይስ ቤተ ክርስቲያን? ክርስቶስ እንደሆነ ሁሉ እናንተም ራሳችሁን አስቀድማችሁ ብትሰጡ ሚስቶቻችሁም ራሳቸውን ይሰጡ ዘንድ ይሆንላቸዋል፡፡**

***አስቀድሞ ራሱን የሰጠ ክርስቶስ ነው***

- **ከኃጢአት በቀር በባሪያ መልክ ሆኖ ከኃጢአት ያነጻንና ወደ ቀድሞ ክብራችን ይመልሰን ዘንድ የሚደነቅ ፍቅሩን ሰጠን፡፡**
- **የማይወሰነው እርሱ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወሰኖ እኛን ወደላይ ከፍ ያደርገን ዘንድ ራሱን ዝቅ አድርጎ ወደ እኛ መጣ፡፡**

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

***አስቀድሞ ራሱን የሰጠ ክርስቶስ ነው…***

- ለቤተ ክርስቲያን ሲል ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ሰጠ፡፡ እስከዛሬም በመስቀል ላይ የፈሰሰውን የከበረውን ደሙን ያፈስላታል፡፡ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከመንፈሱ ጋር ትሆን ዘንድ እስከሞት ድረስ ፍቅሩን ሰጣት፡፡ ለቤተ ክርስቲያኑ ዘላለማዊ ሕይወትን ይሰጥ ዘንድ በፈቃዱ ሞተ፡፡
- ሙሽራይቱ በክርስቶስ ምትክ በርባን ይኖር ዘንድ በፈቀደችበት ያለመታመን ዘመን እንኳ ሳይቀር ወሰን የሌለውን ፍቅሩን ሰጥቷታል፡፡ ስለርሷም ‹‹የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው፡፡›› *ሉቃ 23፡34፡፡* በማለት የባሕርይ አባቱን አብን ጠይቋል፡፡
- የባል የሚስት ራስ መሆን ክብር ብቻ ሳይሆን ኃላፊነትም ነው፡፡ ባሎች ሆይ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምንን በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንደሰጠ መርምሮ በመረዳት የባልነት ኃላፊነታችንን እንዴት መወጣት እንዳለብን ከእርሱ እንማር፡፡
- ባሎች ሆይ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እስኪ ራሳችንንነ እንጠይቅ! በድካምዋና በችግርዋ ጊዜ፣ ስታናድደንም ይቅር እንላታለን? በዚህ ሁኔታ ውስጥስ ሆነን ጌታችን በብረት ችንካሮች ተቸንክሮ በሥጋው ወራት ይጸልይልን እንደነበረ ሁሉ እንጸልይላታለን?

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

***አስቀድሞ ራሱን የሰጠ ክርስቶስ ነው…***

- ባሎች ሆይ! ሚስቶች መሥዋዕትነት ያለበትን ፍቅር እንዲሰጡን ከመጠየቅ በፊት ሁሉን ማፍራት የሚቻለውን ንጹሕ፣ መሥዋዕትነትና ይቅርታ ያለበትን ፍቅር ለሚስቶች እንስጥ፣
- ባሎች ሆይ! የሚስቶች ራስ መሆንን ከሰውነት ጋር ተዋህዶ እንዳለ ራስ ከሚስቶች ጋር እንደ አካል በመሆን ራሳችሁን በመስጠት ሚስቶች ራሳቸውን እንዲሰጡ ምክንያት ከመሆን ጋር ትፈጽሙታላችሁ?
- በርግጥ ሰውነት የሚታዘዘው ከራስ ለመጣለት ትእዛዝ ነው፡፡ ይህን በጥቂቱ እንዲህ እንመልከተው፡-
    - ራስ ከሰውነታችን ሁሉ በላይ እንደሚገኝ ባልም በመንፈስና በአእምሮ ከሚስቱና ከቤተሰቡ በላይ ነው፡፡
    - ራስ የስሜትና የፈቃዳችን ማዕከል እንደሆነ ሁሉ ባልም ይልቁኑ ለሚስቱ እንዲሁም ለቤተሰቡ ፍላጎት መሟላት ጥንቁቅና ተንከባካቢ መሆን ይገባዋል፡፡
    - ለሰውነታችን የሚያስፈልገው ምግብና ውሃ መግቢያው በራስ እንደሆነ ሁሉ ባልም ለቤተሰቡ ይልቁንመ ለሚስቱ የምግብና የእርካታ ምንጭ መሆን አለበት፡፡ ይህም እንካታ አካላዊ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁኑ ስሜታዊና መንፈሳዊ እርካታ እንጂ፡፡ በዚህም መንገድ ፍቅሩና ርኅራኄው ወደሌላው (ቤተሰቡ) በዝቶ ይፈሳል፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

***… አስቀድሞ ራሱን የሰጠ ክርስቶስ ነው…***

- … በርግጥ ሰውነት የሚታዘዘው ከራስ ለመጣለት ትእዛዝ ነው፡፡ ይህን በጥቂቱ እንዲህ እንመልከተው…
    - ራስ የምናይበት ሕዋሳችን የሚገኙበት አካል እንደሆነ ሁሉ ባልም የሚገጥሟቸውን ችግሮች ሁሉ የሚፈታበት መንፈሳዊነትና ብስለት ያለበት አመለካከት የሞላበት ጥበብ እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡
    - ራስ የምንናገርበት ብቻ ሳይሆን የምንሰማበትም ሕዋስ የሚገኙበት አካል እንደሆነ ሁሉ ባልም በቅድሚያ በአግባብ መስማት የሚችል፣ ሲናገርም ይልቁኑ ሚስቱ ሊሰሙት ፈቃዱ ያላቸው ሆነው እንዲሰሙት የሚቻለው መሆን አለበት፡፡
    - ራስ መላ አካልን የሚመራው አንጎል መገኛ እንደመሆኑ ሁሉ ባልም ቤተሰቡን ሁሉ መምራት የሚቻለው ጥበበኛ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ወገኖቼ ከላይ እንደተገለጸው እናደርጋለን?
- በቤታችን ራስ ከመሆን ጋር የክርስቶስ አካል የሆነች የቤተ ክርስቲያን አባላት መሆናችንን ልብ እንበል፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

***… አስቀድሞ ራሱን የሰጠ ክርስቶስ ነው…***

- **አካል ሁሉ እንደሚያደርገው በርሱ ለምንኖርበትና ለምንቀሳቀስበት እውነተኛ ራስ አካላት እንደሆንና ለዚህም እውነተኛ ራስ አካላት ሁሉ እንደሚያደርጉት የምንታዘዝለት ሆነን እንገኝ፡፡**
- **ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ትእዛዛቱ መሪያችን ከሆኑ የቤታችንና የሚስቶቻችን እውነተኛ መሪና ራስ ሆነን እንገኛለን፡፡ በኛ ውስጥ የሚሠራ ክርስቶስም የተነሳ ሚስቶች ራሳቸውን ይሰጡን ዘንድ ይቻላቸዋል፡፡**
- **ሚስቶች ሆይ! በቤታችሁ መከበርን፣ በባሎቻችሁና በልጆቻችሁ ዘንድ መታመንና በረከትን የምትሹ እንደሆነ ጠቢቡ ሰሎሞን** ‹‹ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቍ እጅግ ይበልጣል። የባልዋ ልብ ይታመንባታል። ምርኮም አይጐድልበትም። ዕድሜዋን ሙሉ መልካም ታደርግለታለች፥ ክፉም አታደርግም። የበግ ጠጕርና የተልባ እግር ትፈልጋለች፥ በእጆችዋም ደስ ብሎአት ትሠራለች። እርስዋ እንደ ነጋዴ መርከብ ናት ከሩቅ አገር ምግብዋን ትሰበስባለች። ሌሊት ሳለ ትነሣለች ለቤትዋም ሰዎች ምግባቸውን፥ ለገረዶችዋም ተግባራቸውን ትሰጣለች። እርሻንም ተመልክታ ትገዛለች ከእጅዋም ፍሬ ወይን ትተክላለች። ወገብዋን በኃይል ትታጠቃለች፥ ክንድዋንም ታበረታለች። ንግድዋ መልካም እንደ ሆነ ትመለከታለች መብራትዋ በሌሊት አይጠፋም።…

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

## *… አስቀድሞ ራሱን የሰጠ ክርስቶስ ነው…*

- … እጅዋን ወደ አመልማሎ ትዘረጋለች፥ ጣቶችዋም እንዝርትን ይይዛሉ። እጅዋን ወደ ድሀ ትዘረጋለች፥ ወደ ችግረኛም እጅዋን ትሰድዳለች። ለቤትዋ ሰዎች ከበረዶ ብርድ የተነሣ አትፈራም፥ የቤትዋ ሰዎች ሁሉ እጥፍ ድርብ የለበሱ ናቸውና። ለራስዋም ግብረ መርፌ ስጋጃ ትሠራለች ጥሩ በፍታና ቀይ ግምጃ ትለብሳለች። ባልዋ በአገር ሽማግሌዎች መካከል በሸንጎ በተቀመጠ ጊዜ በበር የታወቀ ይሆናል። የበፍታ ቀሚስ እየሠራች ትሸጣለች፥ ለነጋዴም ድግ ትሸጣለች። ብርታትና ከበሬታ ልብስዋ ነው በኋላም ዘመን ላይ ትስቃለች። አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች የርኅራኄም ሕግ በምላስዋ አለ። የቤትዋንም ሰዎች አካሄድ በደኅና ትመለከታለች፥ የሀኬትንም እንጀራ አትበላም።» ***ምሳሌ 31፡10-27፡፡*** **በማለት ለተናገረው ቃል ታላቅ ትኩረትን ስጡ፡፡**
- **ሚስቶች ሆይ! በየዕለቱ ባሎቻችሁን ለመርዳትና በደስታ መንፈስ ሆናችሁ ከነርሱም ጋር ለመተባበር ትጣጣራላችሁ? በጥበብስ ቃል ትነጋገራላችሁ? ይህንንም በማድረጋችሁ** ‹‹ ልጆችዋ ይነሣሉ፥ ምስጋናዋንም ይናገራሉ ባልዋ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል። መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ፥ አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ። ውበት ሐሰት ነው፥ ደም ግባትም ከንቱ ነው እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች። ከእጅዋ ፍሬ ስጡአት፥ *ሥራዎችዋም* በሸንጎ ያመስግኑአት። ›› ***ምሳ 31፡28-31፡፡*** **የተባለው ይደርሳችኋል፣ ይደረግላችኋል፡፡**

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

ይቆየን።